Amerigroup

District of Columbia

**የአባል የመምርያ መጽሀፍ ዝመና**

እባክዎትን ይህንን በጥንቃቄ ያንብቡ እና በተመዝጋቢ የእጅ መጽሀፍዎ ውስጥ ያስቀምጡት።

በቅርብ ጊዜ ውስጥ **የእርሶ መብቶች እናየእርሶ ሃላፊነቶች** የሚሉትን የእጅ መጽሀፍ ክፍሎች አሻሽለናል። የተከለሱት ክፍሎች ከዚህ በታች ናቸው።

## የእርስዎ መብቶች

**የሚከተሉት መብቶች አልዎት፣**

- በክብር እና በሰብአዊነት ይስተናገዱ።
- ከሀኪምዎ እና ከአገልግሎት ሰጪዎችዎ ጋር ያለዎ ንግግር ሚስጥራዊ እንደሆነ ይወቁ
- አንድ ህመም ወይም ህክምና እርሶ በሚገባዎ ቋንቋ እንዲብራራልዎ ያድርጉ
- በእንክብካቤዎ ላይ የሚደረገው ውሳኔ ላይ እርዳታ ያድርጉ
- ጫና፣ እርምት፣ ምቾች ለማግኘት ወይም ለማጥቃት ጠቅም ላይ ከሚውል እግድ ወይም ገደብ ነጻ ይሁኑ ይህም በእግድ እና ገደብ ላይ በፌደራል ህግ መሰረት የተቀመጠውን መሰረት በማድረግ። ገደብ ማለት በነጻነት እንዳይንቀሳቀሱ የሚያድርግዎ ነገር ነው። እግድ ማለት ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዲለያዩ የሚያደርግ ነገር ነው።
- ስለ እንክብካቤዎ መረጃን በመጠቀም ውሳኔ ያድርጉ። ይህም የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማብራሪያ እየወሰዱ ላሉ የህክምና አማራጭ ስጋቶች መውሰድ ማለት ነው፡
  - ሙሉ
  - ግልጽ
  - ለመረዳት የሚቻል
- ህክምናን ወይም እንክብካቤን ውድቅ ያድርጉ
- ከአካላዎ ወይም ኬሚካል እግዶች ከድንገተኛ ነገር ውጪ ብቻ ነጻ ይሁኑ
- የጤና ማህደሮችዎን ይመልከቱ እና ለውጥ እንዲደረግ ይጠይቁ
- PCP/PDP ከ Amerigroup DC ኔትወርክ ይምረጡ
- የእርስዎን PCP/PDP መቀየር
- ስለ እንክብካቤዎ ቅሬታ ያስገቡ እና መልስ ያግኙ
- Amerigroup DC አገልግሎት ወይም እቃዎችን ከልክሎት፣ መስጠት አቁሞ ወይም ቀንሶ ከሆነ ፍትሀዊ የሆነ ችሎት ለማግኘት ይግባኝ ይበሉ
- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት እና ግብአቶችን ከሚመርጡት አገልግሎት ሰጪ ያግኙ
- አላስፈላጊ የሆነ መዘገየት ውስጥ ሳይገቡ የጤና እንክብካቤ ያግኙ
- የ ቅድሚያ መመሪያዎች መረጃን ያግኙ እንዲሁም በህይወት ለመኖር የሚያስፈልግ ህክምናን ወይም ለማግኘት ወይም ማግኘት ለመቀጠል አይወስኑ
- የ Amerigroup DC ተመዝጋቢ እና/ወይም የአቅራቢ ዳይሬክተሪ ግልባጩን ያግኙ
- ስለ አገልግሎተ ሰጪዎቻችን መረጃ ያግኙ
- አዲስ የእንክብካቤ እቅድ እስከሚያገኙ ድረስ አሁን እያገኙ ያሉትን ህክምና ይቀጥሉ
- **ከክፍያ ነጻ** የትርጉም እና የማስተርጎም አገልግሎትን በማግኘት እነዚህን አገልግሎቶች ውድቅ ያድርጉ
- **ከክፍያ ነጻ** የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ
- ቀድሞ ፈቃድ መስጠት እንዴት እንደሚሰራ ይማሩ
- አገልግሎቶቹን፣ የፋይናንስ ሁኔታውን እና ሌላ ልዩ ከሀኪሞቻችን ክፍያ የምናደርግበትን መንገድ ጨምሮ ስለ Amerigroup DC መረጃ ያግኙ

DHCF The Department of Health Care Finance INVESTING IN YOUR HEALTH

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

**www.myamerigroup.com/DC**

DC-MHI-0003-19

This program is funded in part by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.

- የደንበኞች እርካታ ዳሰሳ ላይ ክለሳ ያግኙ
- በትዛዝ ለሚሰጡ መድሀኒቶች የ Amerigroup DC “እንደተጻፈው ስጥ” ፖሊሲ ያግኙ
- ሽፋን ያላቸው መድሀኒቶች ዝርዝር ይቀበሉ
- ስለመብቶችዎ እና ሃለፊነቶችዎ ለ Amerigroup DC ጥቆማ ያድርጉ
- ከሚከተሉት የአገልግሎት ጤና አቅራቢዎች ይቀበሉ:
  - አገልግሎት እያሰጡ ያሉ እና ለመድረስ ቀላል የሆኑ
  - የተቀናጀ እና ጊዜውን የጠበቀ እንክብካቤ የሚሰጡ
  - ባህላዊ እምነትዎን የሚያከብሩ
  - የሚያስፈልግዎትን ያክል ትክክለኛ እንክብካቤ ማግኘትዎን የሚያረጋግጡ
- ከ Amerigroup DC, አገልግሎት ሰጪዎች፣ ሰብ ኮንትራክተሮች ወይም ዲስትሪክቱ ምንም አይነት መጥፎ የሆነ አያያዝ ሳያጋጥምዎ መብቶን ይጠቀሙ
- የመብቶች እና ሃላፊነቶችዎን ግልባጭ ያግኙ

## የእርስዎ ሀላፊነቶች

**እርሶ ሃለፊነት ያለብዎ ጉዳይ፡**

- አገልግሎት ሰጪዎችዎን በሰብአዊነት እና በክብር መያዝ
- የ DC Medicaid Managed Care Program እና Amerigroup DC ህጎችን መከተል
- የአልግሎት ሰጪዎን መመሪያዎች መከተል
- ስለ ጤና ሁኔታዎ ለሀኪምዎ እና አገልግሎት ሰጪዎ መንገር
- ከአገልግሎት ሰጪዎ ጋር የትኛው የጤና አገልግሎት ለእርሶ ምርጥ እንደሆነ ለመወሰን እንደ ቡድን መስራት
- ቀጠሮ ወደተቀጠረላቸው ቀጠሮዎች መሄድ
- መሰረዝ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ለሀኪምዎ ቢያንስ ከ 24 ሰአቶች በፊት ቀድመው መንገር
- የሀኪምዎን መመሪያ የማይረዱ ከሆነ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሀኪምዎን መጠየቅ
- የጤና ድንገተኛ ነገር ያጋጠመዎ ከሆነ ብቻ ወደ ድንገተኛ ክፍል መሄድ
- በ እርሶ ጤና ላይ ተጽእኖ የሚያደርሱ ነገሮች ያሉ እንደሆነ ለ PCP/PDP መንገር
- የሚከተሉት ነገሮች ያሉ ከሆነ ለ Economic Security Administration (ESA) እና Amerigroup DC መንገር:
  - እርሶ ወይም የቤተሰብ ተመዝጋቢ ሌላ የጤና መድን ያላችሁ ከሆነ
  - የአድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ለውጦች
  - በቤተሰብዎ ውስጥ ለውጥ ያለ ከሆነ (ሞት ወይም ልደት)
- የጤና ችግሮችዎን ለመረዳት መሞክር እና የህክምና ግቦችን በመፍጠር ሂደት ላይ እርዳታ ማድረግ
- ሀኪምዎ ከዚህ በፊት ህክምና ከሰጡዎ አገልግሎት ሰጪዎች መረጃዎችን ለማግኘት ይችል ዘንድ እርዳታ ማድረግ
- ለ Amerigroup DC በስራ ቦታ ላይ ወይም በአደጋ ምክንያት ቁስለት አጋጥሞዎት ከነበር መንገር